## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

## Commercial Bank of Ethiopia

***ጋዜጣዊ መግለጫ***

***የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) አገልግሎት መጀመር አስመልክቶ የተዘጋጀ***

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህብረተሰቡን በተለያዩ የባንክ አገልግሎቶች በመድረስና የሀገሪቱን የክፍያ ሥርዓት በማዘመኑ ሂደት ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ ከ1,250 በላይ ቅርንጫፎችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመክፈት እንዲሁም 1660-ኤቲኤሞችና 7,241 ፖስ የክፍያ ማሽኖችን አመቺ በሆኑ ስፍራዎች በማስቀመጥ ህብረተሰቡ የባንክ አገልግሎትን በቀላሉ፣ በፍጥነትና ምቾት ባለው ሁኔታ የሚያገኝበትን ሥርዓት አመቻችቷል። ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ደንበኞች በሞባይል እና በኢንተርኔት አማካኝነት የባንክ አገልግሎት ካሉበት ቦታ ሆነው በቀላሉ እንዲያገኙ እያደረገ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በርካታ ዜጎች የተንቀሳቃሽ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። የበርካታ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ይህን መሰረተ ልማት በአግባቡ በመጠቀም ከባንክ አገልግሎት ርቀው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የአገልግሎቱ ዋና ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ተስተውሏል። በሀገራችንም ይህን በርካታ ዜጎችን በባንክ አገልግሎት በመድረስ ረገድ የተመሰከረለትን የሞባይል ስልክን መሠረት ያደረገ የባንክ አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል። በተለይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገልግሎቱን በስፋትና በጥራት ህብረተሰቡ ዘንድ ማድረስ የሚቻልበትን ሁኔታ በማጥናትና በሙከራ አገልግሎት በመፈተሽ እነሆ ወደሙሉ ትግበራ አስገብቷል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) በተሰኘው አገልግሎት ደንበኞች በባንክ ቅርንጫፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሞባይል ስልካቸውን በመጠቀም በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕጋዊ ወኪሎች ማግኘት፣ የአገልግሎት ወይንም የዕቃ ግዢ መፈጸም እና ገንዘብ ለወዳጅ ዘመድ ማስተላለፍ በዋነኚነት ከሚያገኟቸው አገልግሎቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

አገልግሎቱ ለደንበኞች በአማርኛ፣ በኦሮሚኛ፣ በትግርኛ፣ በሱማሊኛ፣ በአፋርኛና በኢንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማስተናገድ እንዲቻል ሆኖ የቀረበ ሲሆን ደንበኞች በቀላሉና በፍጥነት ወደቅርንጫፍ መሄድ ሳይጠበቅባቸው አገልግሎቶቹን ማግኘት ያስችላቸዋል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይህን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የንግድ ድርጅቶችን በመመልመልና ተገቢውን ሥልጠናና ፍቃድ በመስጠት የፋይናንስ ተደራሽነትን የሚያሰፋ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን እያቀረበ ይገኛል። የተመረጡት የንግድ ድርጅቶች የሲቢኢ ብር አገልግሎት ለመስጠት በቅርብ በሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በኩል አስፈላጊ መረጃዎችን አቅርበው መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። የውክልና አገልግሎት ከሚሰጡ የንግድ ድርጅቶች በተጨማሪ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያን በ'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) ከሚቀበሉ የንግድ ድርጅቶች ጋርም ስምምነት ተደርጓል።

የሲቢኢ ብር ደንበኞች የሚያገኙአቸው አገልግሎቶች፡-

- *ገንዘብ ማስተላለፍ፡-* ደንበኞች በሞባይል ስልክ ቁጥራቸው ከተከፈተው የሲቢኢ ብር ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወደሌላ የአገልግሎቱ ደንበኛ ወደሆነም ሆነ ወዳልሆነ ግለሰብ የሞባይል ስልክ ብቻ በመጠቀም ገንዘብ ማስተላለፍ ይችላሉ።
- *ክፍያ መፈጸም፡-* ደንበኞች የሞባይል ስልካቸውን በመጠቀም የአገልግሎት ወይም የዕቃ ግዢ ክፍያ በአካል በመቅረብ ወይም ካሉበት ቦታ ሆነው መፈጸም ይችላሉ።
- *ገንዘብ ማስገባት፡-* ደንበኞች የሲቢኢ ብር ወኪሎች ዘንድ በመሄድ ገንዘብ ወደ ሂሳባቸው ያስገባሉ።
- *ገንዘብ ማውጣት፣* ደንበኞች የሞባይል ስልክ በመጠቀም የትኛውም የሲቢኢ ብር ወኪል ዘንድ በመቅረብ ከሲቢኢ ብር ሂሳባቸው ላይ ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ።
- *የሞባይል ስልክ አየር ጊዜ መሙላት፣* ደንበኞች ከሲቢኢ ብር ሂሳባቸው ላይ የሞባይል ስልክ የአየር ጊዜ መግዛት ይችላሉ።
- *የአውሮፕላን ቲኬት መቁረጥ፣* ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በተገባው ስምምነት መሰረት የ'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) አገልግሎትን በመጠቀም የአየር መንገዱን የጉዞ ትኬት መግዛት ይቻላል።

*የ'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) ደንበኛ ለመሆን*

የሲቢኢ ብር ደንበኛ መሆን ቀላል ነው። ማንኛውም ሰው በሞባይል ስልክ ቁጥሩ *847# ላይ በመደወል አስፈላጊ መረጃዎችን በማስገባት የተወሰኑ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችለውን ሂሳብ መክፈት ይችላል። ሙሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሲቢኢ ብር ደንበኞች የታደሰ መታወቂያ (የቀበሌ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የመንጃ ፈቃድ) እና የተንቀሳቃሽ ስልካቸውን በመያዝ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው የባንኩ ወኪል ሄደው የደንበኝነት ቅጽ በመሙላት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) የተሰኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገልግሎት በቦታና በጊዜ ሳይገደብ የፋይናንስ አገልግሎትን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀደም በርቀት፣

በሚያንቀሳቅሱት አነስተኛ ገንዘብ ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ቅርንጫፍ ለመሄድ ለማይችሉ ወይንም የባንክ አገልግሎት ጨርሶ መጠቀም ላልጀመሩ በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች መልካም አጋጣሚን ይዞ የመጣ አገልግሎት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የህበረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማዳበር፣ የገንዘብ ልውውጡን ለማፋጠንና የሀገሪቱን የክፍያ ሥርዓት ለማዘመን የተያዘውን ሃገር አቀፍ ዕቅድ ከማሳካት አንፃር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) የተሰኘውን የሞባይል ስልክን መሠረት ያደረገውን የባንክ አገልግሎት በሙከራ ደረጃ ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም የጀመረ ሲሆን፣ ከታህሳስ 02 ቀን 2010 ጀምሮ ደግሞ ወደሙሉ ትግበራ ተሸጋግሯል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዚህ አገልግሎት እስካሁን ከ2,660 በላይ አገልግሎቱን የሚሰጡ ወኪሎችን፣ ከ1,350 በላይ የአገልግሎት ወይም የዕቃ ሽያጭ ክፍያን በ'ሲቢኢ ብር' (CBE Birr) በኩል የሚቀበሉ የንግድ ተቋማትን የመለመለ ሲሆን፣ ከ225,980 በላይ ተጠቃሚ ደንበኞችን ማሰባሰብ ችሏል። የወኪሎችን፣ የንግድ ተቋማትን እና የተጠቃሚ ደንበኞችን ቁጥር ለማሳደግ መጠነ ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በአጠቃላይ ባንኩ የሀገራችንን የፋይናንስ አካታችነት (financial inclusion) ለማሳደግና የክፍያ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚረዱ ሌሎች ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በየጊዜው እየቀረጸ መተግበሩን አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል።